
1ኛ ዓመት ቁጥር 2
1 Year No. 2



ባሕር ዳር ሰኔ 15 ቀን 1987 ዓ.ም
Bahir Dar 22nd JUNE 1995

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የ ፖ.ሣ.ቁ 312 P.o.Box

ማውጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 2/1988 የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት ማቋቋሚያ አዋጅ ገጽ 23	Proclamation No-2/1995 A Proclamation to provide for the Establishment of the Constitution of the Amhara National Region Page 23

አዋጅ ቁጥር 2/1988 ዓም

የአማራው ብሔራዊ ክልል

ሕገ መንግስት

መግቢያ

እኛ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝቦች ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየውን ጨቋኝ ሥርዓት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችንን አፍኖ፣ የተዛባ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ለኋላ ቀርነት ዳርጎን መቆየቱ በእድገታችን ላይ ያደረሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማስወገድ በመሻት፣

በአብዛኞቹ የአገራችን ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች ላይ ሲፈጸም የቆየው አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጉዳቱ ሰለባዎች ሆነን መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ እንዲታረም በመፈለግ፣

መላ የአገራችን ብሔር፣ ብሔረሰብ ህዝቦች ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ የነበረው ኃላ ቀር አፋኝ ሥርዓት ተገርስሶ፣ አገራችን ኢትዮጵያ የግለሰብና የህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ የሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰብ ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ የተከበሩባት፣ በአጠቃላይም የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ሪፑብሊክ መሆኗ ለጋራ እድገታችን መፋጠን ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፣

በአማራ ብሔራዊ ክልል የምንገኝ ህዝቦች በተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለዘላቂ ሰላምና ለዳበረ ዴሞክራሲ የምንበቃው ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት የተቀዳ፣ ከክልላችን ሁኔታ ጋር የተገናዘበና የክልሉ ህዝቦች የተከበሩልንን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ባልተሸራረፈ ሁኔታ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ሕገ መንግሥት ሲኖረን እንደሆነ አጥብቀን በማመን፣

ይህን ክልላዊ ህገ መንግስት በቀጥተኛ ተሳትፏችን መርጠን በላክናቸው የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ተወካዮች አማካኝነት ሰኔ 15 ቀን 1987 ዓ.ም አጽድቀነዋል።

የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1

የክልሉ መንግስት ስያሜ

ይህ ሕገ መንግስት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዴሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል። በዚህ መሰረት የሚቋቋመው መንግስት "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት" በሚል ስም ይጠራል።

አንቀጽ 2

የአማራ ክልል ወሰን

የአማራ ክልል በሰሜን ትግራይ ክልል፣በምስራቅ አፋር ክልል፣ በደቡብ

Proclamation No-2/1995

A Proclamation of the Constitution of the Amhara National Region

Preamble

WHERE AS, we the people of the Amhara National Region, desiring to do away with the negative impact, which the age old oppressive system, that suppressed our human and democratic rights, inflicted upon our development through its unb7alanced economic and social policies, there by Subjecting us to poverty and back wardness,

WHERE AS, desiring to rectify the damaging circumstances, caused by the atrocious national oppression once and for all, to which most of the nations, nationality and peoples of our country, were subjected, and which has been directly or indirectly victimizing us;

WHERE AS, realizing that, through the heroic struggle of all the nation, nationality and peoples of our country, the backward oppressive system has been uprooted, and for the benefit of the advancement of our mutual development, our ounty Ethiopia, has now become a federal Democratic Republic, where generally, rule of law has reigned, individual and peoples human and democratic rights, and peoples rights to self determination unto secession, is being respected,

WHERE AS, strongly believing that, we the people of the Amhara Region, shall achieve rapid economic development, sustainable peace, and developed democracy through our own constitution that is adopted from the constitution of the Federal democratic Republic of Ethiopia, intertwined with the objective situation of the region, which shall enable us to exercise our respected and unrestricted constitutional rights.

Now, THEREFORE, we do hereby adopt this regional constitution on this 22nd day of June 1995, through our representatives elected with our direct participation for the council of the Amhara National Regional State,

ኦሮሚያ ክልል በምዕራብ የቤኒሻንጉል /ጉምዝ/ ክልልና ሱዳን ያዋስኑታል።

አንቀጽ 3

የአማራ ክልል ብሔራዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ

የአማራ ብሔራዊ ክልል የራሱ ሰንደቅ ዓላማና አርማ ይኖረዋል፣ ዝርዝራም በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 4

የአማራ ክልል ብሔራዊ መዝሙር

የአማራ ክልል የራሱ ብሔራዊ መዝሙር ይኖረዋል።
ዝርዝራም በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 5

ስለ ቋንቋ

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ቋንቋዎች በመንግስት እኩል ዕውቅና ይኖራቸዋል።
2. አማርኛ የክልሉ ብሔራዊ መንግስት የሥራ ቋንቋ ይሆናል

አንቀጽ 6

የክልሉ - ርዕሰ ከተማ

የክልሉ ርዕሰ ከተማ ባሕር ዳር ነው።

አንቀጽ 7

የዕታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ መንግስት ውስጥ በወንድ ዕታ የተደነገገው የሴቷንም ዕታ ያካትታል።

ምዕራፍ ሁለት

የሕገ መንግስት መሠረታዊ መርሆዎች

አንቀጽ 8

የሕዝብ ወሳኝነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. የአማራው ክልል ሕዝቦች የክልሉ ብሔራዊ መንግስት የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው።
2. የሕዝቦች የበላይነት የሚገለጸው በሚመርጧቸው ተወካዩችና ራሳቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው።

አንቀጽ 9

የሕገ መንግስቱ የላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. ይህ ሕገ መንግስት የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የማንኛውም የመንግስታዊ አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግስት ጋር ሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈጻሚነት አይኖረውም።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪዎች፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማሕበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።

3. በዚህ ሕገ መንግስት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥትን ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

አንቀጽ 10

ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።
2. የዜጎችና የሕዘቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

አንቀጽ 11

የመንግሥትና ሃይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።

CONSTITUTION OF THE AMHARA NATIONAL REGION

CHAPTER ONE

GENERAL PROVISIONS

ARTICLE 1

THE NAME OF THE REGIONAL STATE

This constitution provides for the democratic structure of the Amhara National Regional State Accordingly, the National State shall be called `the Amhara National Regional State''

The state to be established according to this shall be called "The Amhara National Regional State''

Article 2

Territory of the Amhara Region

The Amhara region is bordered by the Tipray region in the North, the Afar region in the East, The Oromiya region in the South, the Benshangal (Gumuz) region and the Sudan in the West,

Article 3

Flag of the Amhara National Regional State

The Amhara National Region State shall have its own flag and emblem; the particulars shall be determined by law.

Article 4

The National Anthem of the Amhara Region

The Amhara Region shall have its own national Anthem; the particulars shall be determined by law.

Article 5

Language

1. All languages existing in the region, shall enjoy equal state recognition
2. The official language of the regional state shall be Amharic

Article 6

Capital city of the Region

Bahir Dar is the capital city of the region.

2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖት በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

አንቀጽ 12

የመንግስት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።
2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል፣ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
3. ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል።

ምዕራፍ ሶስት

መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

አንቀጽ 13

ተፈጻሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የብሔራዊ ክልሉ መንግስት የሕግ አውጭ፣የሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት የመሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌዎች የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ከተቀበላቸው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች፣ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ሰነዶች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።

ክፍል አንድ

አንቀጽ 14

የአማራው ሕዝብ ብሔራዊ መብቶች

የአማራው ሕዝብ ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚህ መሠረት የአማራው ብሔር ሕዝብ፣

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ እንደሁም በቋንቋው የመጠቀም፣ቋንቋውን የማሳደግ፣ባህሉን

የመግለጽ፣የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው፣

2. በራሱ መልከዐ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመጨረስ፣ራሱን በራሱ የማስተዳደርና እንዲሁም የማዕከላዊ መንግስት ውስጥ በነፃነት፣ አድልዎ በሌለበት፣ተገቢና ርትዓዊ በሆኑ የውክልና አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ መብት አለው።

3. የአማራው ብሔር ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት፣ ሕዝቡ

Article 7

Gender

In this constitution, provisions enacted in the masculine gender shall be deemed to include the feminine gender

CHAPTER TWO

FUNDAMENTAL CONSTITIONAL PRINCIPLES

Article 8

The Determination of people

With out prejudice to the super macy of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,

1. The supreme power of the Regional state, belongs to the peoples of the Amhara Region,
2. The Supre macy of the people shall be expressed through their elected representatives and through their direct democratic participation.

Article 9

Sure macy of the Constitution

Without prejudice to the sure macy of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

1. This constitution is the supreme law of the national Region. Any law, customary practice, and decision, made by state organ or public official inconsistent there with shall be null and void
2. All residents, state organs, political organizations, other associations and their officials, have the duty to comply with this constitution; and have it respected;
3. Assuming power in any manner, other than as provided by this constitution is prohibited.

Article 10

Human and Democratic Rights

1. Human rights and freedoms as inherent rights of man are inalienable and inviolable.
2. The Human and Democratic rights of peoples and citizens, shall be protected.

Article 11

Separation of State and Religion

1. The Amhara National Regional State is a secular state
2. There shall be no state religion
3. The state shall not interfere in

በሰፈረበት መልክዐምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌደራል መንግሥቱ አስተዳደር ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።

4. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር ከ1-3 የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ፣ተረገጡ፣ወይም ተሸራረፉ ብሎ ባመነበትና ባንድነት ስር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 39 በተደነገገው መሠረት የራሱን እድል በራሱ እስከመገንጠል ድረስ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል።

5. የብሔር ፣ብሔረሰቦች፣ሕዝቦች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ያላቸውን የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል ድረስያለ መብት በሥራ ላይ የሚውለው፣

ሀ. የመገንጠል ጥያቄ በብሔር ብሔረሰብ ወይም በሕዝብ የሕግ አውጭ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ የድምጽ ድጋፍ የተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣

ለ. የፌደራሉ መንግስት የብሔር ብሔረሰብ ወይም የሕዝብ ምክር ቤቱ የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር ብሔረሰብ ወይም የሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፣

ሐ. የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝብ ውሳኔው በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፣

መ. የፌደራሉ መንግስት መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር፣ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ፣

ሠ. በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ርክክብ ሲደረግ ነው።

6. በአንቀጽ 14 በንዑስ አንቀጽ 1-5 የተጠቀሱት ብሔራዊ መብቶች በክልሉ ውስጥ ላሉት ለኽምራ፣ለአዊና ለኦሮሞ ሕዝቦች ይሠራል።

7. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ብሔር፣ብሔረሰብ፣ሕዝብ ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጹትን ባህርያት የሚያሳይ ማህበረሰብ ነው። "ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑና የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸው እንዲሁም በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓምድር የሚኖሩ ናቸው"

religious affairs, neither shall religion interfere in the affairs of the state

Article 12

Functions and Accountability of state

1. The activities of state shall be undertaken in a manner which is open and transparent to the public.
2. The people may recall any one of their representatives, whenever they loose confidence in him; the particulars shall be determined by law.
3. Any public official or elected representative, shall be accountable for breach of his official duties

CHAPTER THREE

Fundamental Rights and Freedoms

Article 13

Scope of Application and Interpretation

1. The legislative, executive and judicial branches of the National Regional State, at all level, shall have the duty to comply with the provisions of this chapter, and have it respected.
2. The Fundamental rights and freedoms enumerated in this chapter shall be interpreted in a manner consistent with the universal declaration of Human rights; international human rights, covenants, and conventions, ratified by the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

PART ONE

ARTICLE 14

National Rights of the Amhara People

The Amhara Peoples as provided in the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, shall have the unrestricted right to self determination up to secession.

Accordingly, the people of the Amhara Nation;

1. Shall, have the right to preserve and have it respected, its national identity to preserve and promote its history and heritage, as well as, to use and develop its language; to promote its culture, help it grow and flourish.

ክፍል ሁለት

ሰብዓዊ መብቶች

አንቀጽ 15

የሕይወት፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈ የማይገሰስ፣የሕይወት የመኖር፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

አንቀጽ 16

የሕይወት መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፣ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

አንቀጽ 17

የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

አንቀጽ 18

የነፃነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ወንድም ሆነ

ሴት ነፃነቱን /ነፃነቷን/ አያጣም /አታጣም/።

2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

አንቀጽ 19

ኢሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሰራ ማድረግ የተከለከለ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት" የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም።

ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንደሰራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራው ማንኛውም ሥራ፣

ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትኩ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ሐ. የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ የሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥን ማንኛውም አገልግሎት፣

መ. በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በኣካባቢው የሚፈጸምን ማንኛውም የኢኮኖሚና የማኅበራዊ የልማት ሥራ።

አንቀጽ 20

የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈጽመዋል የሚባሉ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶች በዝርዝርና ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ

እንዲነገራቸው መብት አላቸው።

2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው።
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ስዓታት ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህም ጊዜ ሰዎች ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት አላቸው።
4. የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደብ መሠረት ፍርድ ቤት በመቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ፣ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው። ሆኖም ፍትሕ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።
5. የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል

የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማንኛውም ማስርጃ እንዲያምኑ

2. Shall, have the unrestricted right to determine and administer its own affairs on its own, within its geographical area, as well as, the right to participate freely and effectively in a manner of fair and proper representation in the central government.
3. The Amhara Nation shall, have the unrestricted right to administer itself; and this shall include the right to establish governmental institutions within the territory it inhabits, and the right to fair representation in the federal government.
4. Shall, exercise its right to self determination up to secession, in accordance with article 39 of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; where it is convinced that, the rights mentioned in sub article 1-3 of this provision are denied, abridged, or abrogated, and could not be rectified, under unity.
5. The right to self determination up to secession of nation, nationality and peoples, stipulated in sub article 4 of this provision, may be exercised;

a/ Where the demand for secession is approved by a two-thirds (2/3) majority vote of the legislative council of the nations nationalities or peoples.

b/ where the federal state organizes referendum for the nation nationality or the people demanding secession with in three years upon receipt of the rsion of the council of the nation nationality or People.

c/ Where the demand for secession is supported by a simple majority vote in the referendum,

d/ Where the Federal Government transfers power to the parlianent of the nation, nationality or people which has opted for secession,

e/ Where property is partitioned in accordance with the law,

6. The National Rights enumerated in sub. articles 5 of article 14 shall be applicable to the peoples of HIMRA; AWI and

አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

6. የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፈታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

አንቀጽ 21

የተከሰሱ ሰዎች መብት

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኃላ ተገቢ በሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ መደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው። ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት፣የሕዝቡን የሞራል ሁኔታና የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸውና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው።
3. በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር፣በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው።
4. የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣

ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።

5. በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው።
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጣቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው።
7. የፍርድ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።

አንቀጽ 22

በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ሥር የሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው።
2. ከትዳር ጓደኞቻቸው ፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸውና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው።

አንቀጽ 23

የወንጀል ሕግ ወደ ኃላ ተመልሶ የማይሰራ ስለ መሆን

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኃላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

አንቀጽ 24

በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

OROMIA

7. The term '' Nation, Nationality or people in this constitution'' Shall mean " a community with the following characteristics " People with culture reflecting common charactterstic features or similar custom, common language, in which they can communicate, who belive that they have a common or related life and who have a common psychological make up as well as the majority of whom live with in a common territory''

PART TWO
Human Rights
Article 15
The Right to Life, Liberty and Security of Person

Every one by virtue of being human has the inalienable and inviolable right to life, liberty, and security of person.

Article 16
The Right to Life

Every human being has the right to live. No one shall be deprived of his life except by reason of his conviction in accordance with the law, for a serious crime committed by him.

Article 17
The Right to Security of Person

Every one shall have the right to security of person

Article 18
Liberty

1. No one whether male or female shall be deprived of his (her) liberty except in accordance with such procedures as are

ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግና ሥነሥርዓት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

አንቀጽ 25

የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስም የመከበር መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው።
3. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው።

አንቀጽ 26

የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸው ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህረገድበዘር፣በብሔር/ብሔረሰብ፣በቀለም፣በፆታ፣

በቋንቋ፣በሃይማኖት፣በፖለቲካበማኅበራዊአመጣጥ፣በሀብት፣በትውልድ፣ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

አንቀጽ 27

የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለን ንብረት የመያዝና የመጠበቅ መብትን ያካትታል።
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚግባባቸው፣በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሚኒኬሽን በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።
3. የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብን ሰላም፣ ወንጀልን በከላከል፣ጤናንና የሕዝብን የማራል ሁኔታ በጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሠረቱ ዝርዝር ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

አንቀጽ 28

የሃይማኖት፣የእምነትና የአመለካከት ነፃነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣የሕሊና እና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣የመከተል፣የመተግበር፣የማስተማር ይም የመገለጽ መብትን ያካትታል።
2. በአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችላቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአሰተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ።
3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት

laid down by law.

2. No one shall, be arrested or detained with out being charged or convicted of a crime except in accordance with such procedures as are laid down by law.

Article 19

Prohibition of Inhuman Treatment

1. Every one shall, have the right not to be subjected to cruel, inhuman or degrading treatment or punishment
2. No one shall, be held in slavery or servitude trafficking in human being for whatever purposes it might be is prohibited.
3. No one shall, be required to perform forced or compulsory labour
4. For the purpose of sub article 3 of this provision, the term '' forced or compulsory labour shall" not include,
   a/ Any labour which is in accordance with the law, required of a prisoner while in detention or of a person during conditional release from such detention
   b/ any service required of a person who is a conscious objector in lieu o military service
   c/ Any service exacted in cases of emergency or calamity threatening the life, or well being of the community;
   d/ Any voluntary economic or social developmental activity undertaken by the people of the community concemed;

Article 20

Rights o Persons under Arrest

1. Any one arrested on criminal charges shall, have the right to be informed promptly and in detail, in a language which he understands of the nature and cause of the charge against him;
2. Every one under arrest shall, have the right to keep silent and to be warned promptly, in a language which he understands, that any statement he may

በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በሰገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።

4. ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ-ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።

5. ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣የሕዝብን የሞራል ሁኔታ፣የሌሎች ዜጎችን መሠታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በማወጡ ሕጎች ይሆናል።

አንቀጽ 29

በሰብዕና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ባፀደቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች የሰው ዘር የማጥፋት፣ያለፍርድ የሞተ ቅጣት አርምጃ የመውሰድ፣በአስገዳጅ ሰውን የመሰወረ ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይም በይቅርታ አይታለፋም።

ክፍል ሶስት

ይሞክራሲያዊ መብቶች

አንቀጽ 30

አመለካከትና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።
2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣በስነጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውንም የማስራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም አይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።
3. የኘሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የስነጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የኘሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል።
   ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑ፣
   ለ/ የህዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን፣
4. ለይሞክራሲያዊ ስርአት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ኘሮስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል።
5. በመንግስት ፕንዙብ የሚካሄድ ወይም በንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።
6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣የሰውን

make may be used in evidence against him,

3. Every one shall, have the right to be brought before a court of law within 48 hours after his arrest. This shall not include, a reasonable time taken in the journey to a court of law. He shall, have the right to be specifically informed that there is sufficient cause for his arrest, as soon as, he appears in court;
4. Every one shall, be entitled to an inalienable right of habeas corpus where the police officer or the public prosecutor fails to bring the accused to court within the time limit provided by law where the interest of justice so requires or where remand has been requested for further investigation the court may order the accused to be kept in custody for a duration as is deemed necessary Remand granted by a court shall, be such as to enable the responsible officials of the public prosecution, to investigate and speedily bring the case to a court of law
5. Persons under arrest shall, have the right not to be forced to make any confessions or admissions of any evidence, that may be brought against him during the trial. No evidence obtained in such a manner shall, be legally admissible
6. Any one under arrest shall, have the right to be released on bail. The courts may, however, for reasons specified by law, reject the application for bail, allow a conditional release, or demand the production of sufficient sureties.

Article 21

Rights of the Accused

1. Every one charged with an offence shall, be entitled to a public hearing before an ordinary court of law with out undue delay, the trial may however be conducted in camera only for the purposes of protection the private lives of the parties public morals, and moral

ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ። ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ህጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

አንቀጽ 31

የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። አቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በህዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ደሞክራሲያዊ መብቶችና የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ስርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ህጎች መሰራት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

አንቀጽ 32

የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባባ ያለውን ሕግ በጣስ ወይም ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በህገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

አንቀጽ 33

የመዘዋወር ነፃነት

ማንኛውንም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖርያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለው።

አንቀጽ 34

የሌሎች ክልሎች ተወላጆች መብት

1. የሌሎች ክልሎች ተወላጆች የሆኑ ኢትዮጵያውያን በዚህ ክልል ውስጥ እንደማንኛውም የዚህ ክልል ተወላጅ ሰርቶ የመኖር፣ የሥፍራ ሥፍራ በነፃ የመዘዋወርና ሀብትና ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብት አላቸው።
2. የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የክልሉ ሕዝባዊና መንግስታዊ ሥራ ውስጥ ተመርጦ ወይም ተመድቦ ለመስራት መብት አለው።

አንቀጽ 35

የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ መንዶችና ሴቶች

security

2. Every-one charged with an offence shall, be adequately informed in writing of the charges brought against him.
3. Everyone charged with an offence shall, be presumed innocent until proved guilty, by a court of law; and not to be compelled to testify against himself
4. Every one charged with an offence shall be entitled to inspect any evidence brought against him, examine

witnesses testifying against him, present or obtain the production of any evidence or obtain the attendance of witnesses in their defence

5. Every one charged with an offence shall, have the right to defend himself through legal assistance of his own choosing, and to have freel legal assistance assigned to him by the government, where the interests of justice so requires, and he does not have sufficie nt means to pay for it.
6. Every one charged with an offence shall, have the right to his conviction or sentence being reviewed on appeal, by a competent court of law
7. Everyone charged with an offence shall, have the right to be provided with an interpreter by the government, where the trial is conducted in a language which he does not undrstand.

Article 22

Rights of Persons in Custody and Convicted Prisoners

1. Any person in custody or a convicted prisoner shall, have the right to humane treatment which accords with his human dignity.
2. Any person in custody or a convicted prisoners shall, have the right to communicate with and be visited by spouse (s), close relatives and friends, medical attendants, religious and legal counsellors.

Article 23

None – Retroactivity of Criminal laws

1. No one shall, be held guilty of any criminal

በዘር፣በብሔር፣በብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈጻጸም ፣በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍቺም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ።

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሠረታል።
3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ከሕብረተሰቡና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።
4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖት፣በባሕልና በሕግ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።
5. ይህ ህገ መንግስት የግልና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ ፣በሃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 36

የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ህገ መንግስት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
2. ሴቶች በዚህ ሕገ-መንግስት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። ከዚህ አኳያ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዮ ትኩረት ለመስጠት ነው።
4. ሴቶች ከጎጅ ባሕል ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግስት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ፣ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው።
5. ሀ/ ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደሞዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፣ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል።

ለ/ የወሊድ ፈቃድ በሕግ የሚወሰነው መሠረት ከሙሉ የደሞዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል።

6. ሴቶች በብሔራዊ ክልሉ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በንሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ንሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
7. ሴቶችንብረትየማፍራት፣የማስተዳደርየመቆጣጠር፣የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።
8. ሴቶች የቅጥር፣የሥራ እድገት፣የእኩል ክፍያን ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው።
9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ

offence on account of any act, or omission, which did not constitute a criminal offence under the law at the time when it was committed. Nor shall, a heavier penalty be imposed than the one that was applicable at the time when the criminal offence was committed

2. Not withstanding the provisions of sub article 1 of this article, laws enacted after the commission of the offence shall, apply before or after sentence where they are favourable to the accused.

Article 24
Prohibition of Double Jeopardy

No one shall, be liable to the tried or submitted again for an offence for which he has been finally convicted, or acquitted, in accordance with the criminal laws and procedures.

Article 25
Right to Human Dignity and Good Reputation

1. Everyone shall, have the right to his human dignity and good reputation
2. Every one shall, have the right to freely develop his personality in a manner consistent with the rights of others.
3. Every one shall, have the right to recognition every where as a natural person, before the law.

Article 26
The Right to Equality

All persons shall be equal before the law, and shall, be entitled to equal protection of the law, with out any discrimination what soever. All persons, shall be entitled to equal and adequate guarantees without

distinction of any kind; such as race, nation, nationality colour sex language religion

ትምህርት መረጃና አቅም የማግኘት መብት አላቸው።

አንቀጽ 37

የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት።

ሀ/ በሕይወት የመኖር፣

ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ/ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ/ ጉልበትን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከሥራት የመጠበቅ፣

ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በካሉ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፣

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች፣ ወይም በሕግ አውጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።

3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግስት እርዳት የሚያድጉ ወጣቶች በመንግስት ወይም እንለ ማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።

4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው።

5. መንግስት ለእንለ ማውታን ልዩ ጥበቃ ያደረግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል።

አንቀጽ 38

ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ውሳኔ ወይም ፍርድ፣

ሀ/ ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ/ ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

አንቀጽ 39

የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣በዘር፣በብሄር፣በብሄረሰብ፣ በፆታ፣በቋንቋ፣በሃይማኖት ፣በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ለይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት

ሀ/ በቀጥታና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በህዝብ ጉዳይና አስተዳደር የመሳተፍ፣

political or social origin, property, birth or other status

Article 27

Right to privacy

1. Every one shall, have the right to his privacy and physical integrity. This right shall, include protection from searches of his person, his home, his property and protection from seizure of property under his possession.
2. Private postal correspondence, as well as, other communication through the telephone telecommunications and other electronic device, shall be inviolable
3. Government officials shall, have the duty to respect and enforce these rights Exercise of these rights may only be restricted by laws enacted for purpose of prevention of crimes, protection of national security, public health and morality, rights and freedoms of others, in periods of emergency.

Article 28

Freedom of Religion, Conscience and Thought

1. Every one shall, have the right to freedom of thought, conscience and religion. This right shall, include freedom, either individually or in community with others, and in public or in private, to manifest his religion or belief in worship, observance practice and teaching.
2. Without out prejudice to subarticle 2 of article 96 of this constitution, followers of any religion in order to enable them disseminate and organize their religion, may establish educational and administrative institutions.
3. No one shall, be subject to coercion by force or any other means, which would impair his freedom to have or to a adopt a religion or belief of his choice,
4. Parents and legal guardians shall have, the rights, in accordance with their belief to give their children religious or moral instruction.

ለ/ እድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በህግ መሰረት የመምረጥ፣

ሐ/ በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄደው የመንግስት ምርጫ የመመረጥና የመምረጥ፣ ምርጫው ሁሉን አቀፍ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና መራጩ ፍቃዱን በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ በነፃነት የሚገልጽበትን ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት፣

2. በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሰራተኞች በንግድ አሰሪዎችና በሙያ ማህበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ፍላጎቱና አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ በሀላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆኑ ድረስ በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 40
የንብረት መብት

1. ማንኛውም በክልሉና በክልሉ ውጭ የሚኖር/የምትኖር ኢትዮጵያዊ/ዊት የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/ኗ ይከበርለታል/ላታል፣ ይህ መብት የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም፣ ወይንም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።

2. ለዚህ አንቀጽ አላማ "የግል ንብረት" ማለት ማንኛውም በክልሉና ከክልሉ ውጭ ነዋሪና ኢትዮጵያዊ ወይም ህጋዊ ሰውነት በህግ የተሰጣቸው አገር አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ማኅበራት፣ ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በህግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤቶች እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በፈጠራችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው፣ የአፈሩትን ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።

3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ ሕዝብ የጋራ ንብረት ነው።

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው። አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

5. በክልሉ የሚገኙ ዘላኖች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነጻ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው። አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል።

6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግስት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩም በሕግ ይወሰናል።

7. ማንኛውም በክልሉና ከክልሉ ውጭ ነዋሪና ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል።

5. Freedom to manifest one's religion or belief, may be subject only to such limitations as are prescribed by law; and are necessary to protect public safety, order, health, or morals, or the fundamental rights and freedoms of others, and to ensure the secular nature of the state.

Article 29
Crimes Against Humanity

There shall, be no period of limitation on persons charged with crimes against humanity, as provided by international conventions ratified by Ethiopia, and other laws of Ethiopia. The legislature or any other organ of state shall, have no power to pardon, or give amnesty, with regard to such offences.

PART THREE
DEMOCRATIC RIGHTS

Article 30
Right to hold Opinions, Thoughts and Free Expressions.

1. Every one shall have the right to hold opinions with out any interference
2. Every one shall, have the right to freedom of expression with out interference This right shall include: freedom to seek, receive, and impart, information and idea of all kinds, regardless of frontier, either orally, in writing or in print, in the form of art or through other media of his choice.
3. Freedom of the press and mess media and freedom of artistic creation, is guaranteed. Press freedom shall, in particular, include the rights enumerated hereunder,

a/ That censorship in any form is prohibited

b/ The opportunity to have access to information of interest to the public

4. The press shall, be granted institutional independence and legal protection, to enable it accommodates different opinions. and ensure the tree flow of information,

ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል።

8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረቱን ለመውሰድ ይችላል።

አንቀጽ 41
የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደርያው የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት አለው።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።
3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግስት ገንዘብ በሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።
4. የክልሉ መንግስት የጤና፣የትምህርትና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።
5. የክልሉ መንግሥት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣

ideas and opinions, that are necessary in a democratic society

5. Any media financed or controlled by the government shall, be organized in a manner suitable for the accommodation of differences of opinions

6. The above mentioned rights may be subjected to limitations only in such laws issued based on the principle that, the freedom to seek opinion and information shall not be deprived owing to the content and the effect of thought to be followed there of legal limitations may be laid down upon these right only for the sake of protecting the wellbeing of youth, human

አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።

6. የክልሉ መንግስት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ኘሮግራሞችን ያወጣል፣ ኘሮጀክቶችን ያካሂዳል።
7. የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይዋስዳል።
8. ገበሬዎች እና ዘላኖች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሔራዊ ሀብት ካደረጉት የምርት አሰተዋፅዖ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው። የክልሉ መንግሥት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።
9. መንግስት የባሕልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብ፣ለሥነ ጥበብ እና ለሰፖርት መስፋፋት አስተዋፅዖ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

አንቀጽ 42
የሠራተኛ መብት

1. ሀ. የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች፣ ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች፣ የሣራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትንና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት፣ከአሰሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን የካትታል።

ለ/ በንዑስ አንቀጽ ሀ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታ የማሰማት መብት አላቸው።

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ ሀ እና ለ መሠረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የማችሉት የመንግስት ሰራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።

መ/ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት

dignity and good reputation Agitation for war. as well as public statements against human dignity shall be prohibited by law Any citizen found violating these legal limitations in exercising the above mentioned rights shall. be liable to law

Article 31
Freedom of Assemble, Public Demonstration and the Right to Petition

1. Every one shall; have the freedom, in association with others, to peaceably assemble with out arms, engage in public demonstration; and the right to petition. Appropriate procedures may be enacted to ensure that, public meetings and demonstrations do not disrupt public activities; or that such meetings and demonstrations do not violate public morals, peace, and democratic rights.
2. This right shall not absolve any one of liability arising from the laws enacted to protect the safety of the youth, human dignity, and good reputation, aspiration for war and public statements that affect

መብታቸው የተጠበቀ ነው።

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍል ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።

3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ።

አንቀጽ 43

የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
2. የክልሉ ነዎሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ኘሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል።

አንቀጽ 44

የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንጽሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመሮ መብት አላቸው።
2. የክልሉ መንግስት በሚያካሂዳቸው ኘሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ የመንግስትን በቂ እርዳታ፣ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ ኘንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

ምዕራፍ አራት

የክልሉ መንግስት አወቃቀርና የሥልጣን አከፋፈል

አንቀጽ 45

የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. ክልሉ በክልል፣በዞኖች፣ በወረዳዎችና በቀበሌዎችየተዋቀረ ነው። ይሁን እንጅ የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጉ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖች ሊያዋቅርና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ይችላል።
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኝ የኽምራ፣የአዊና የኦሮሞ ሕዝቦች የራሳቸው የዞን ምክር ቤት ይኖራቸዋል።
3. በክልሉ ውስጥ የማገኙ የሌሎች ብሔረሰብ ሕዝቦች ውክልና በልዩ ሁኔታ የሚታይ ይሆናል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

human dignity.

Article 32
Right to Association

Everyone shall have the right to form associations for whatever purposes Associations formed in violation of the appropriate laws, or Associations formed with the objective of overthrowing the constitutional order, or associations carrying out these activities, shall, be prohibited.

Article 33
Freedom of Movement

Every resident of the region or any other preson lawfully within the region shall, have the freedom to freely move and establish his residence within the region; as well as, to travel out of the region.

Article 34
Rights of persons of other Regions

1. Any Ethiopian citizen of other regions, residing in this region, shall have the right to live and work, to move freely from place to place to posses and own property and wealth as other people of the region.
2. Any Ethiopian who speaks the language of the region, shall, have the right to be elected or placed in any governmental or public offices.

Article 35
Rights relating to Marriage, the Individual, and the Family

1. All men and women attaining the legal age of marriage, shall, have without any distinction as to race, nation, nationality or religion, the right to marry and form a family They shall have equal rights in the process of contracting the marrinage, its duration, and dissolution Regulations shall

አንቀጽ 46
የክልሉ የሥልጣን አካላት አወቃቀር

1. የክልሉ መንግሥት ሕግ አውጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱም ለወከለው ሕዝብ ነው።
2. የክልሉ ከፍተኛ ሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲሆን ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የክልል የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤት ብቻ ነው።

አንቀጽ 47
የክልል ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግስት ውስጥ በውል ተለይተው ለፌደራሉ መንግስት ከተሰጡት ሰልጣንና ተግባራት ውጪ ያለ ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግስት ሥልጣንና ተግባር ይሆናል።
2. በዚህ መሰረት ክልላዊ ንግስቱ፣
2.1 የክልሉን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጅና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣
2.2 የክልሉን ህገ መንግስትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል ያስፈጽማል
2.3 የፌደራሉ መንግስት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፣
2.4 ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት ይገነባል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክና የክልሉን ሕገ መንግስት ይጠብቃል፣ ይከላከላል።
2.5 ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፣ በጀት ያወጣል፣ ያስፈጽማል።
2.6 የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያውጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣የስልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።
2.7 የክልሉን ፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ይመራል፣የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል።
2.8 በሕግ መሠረት ይቅርታ ያደርጋል።
2.9 በክልል መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ይሰበስባል።
2.10 የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወሰናል፣ ይሰበሰበል።
2.11 የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል ይሰበስባል።
